# የብልጽግና ፓርቲ የተኪ አመራር ምልመላ ማስፈፀሚያ መመሪያ

ሚያዝያ/2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ይዘት


መግቢያ ........................................................................................................1

ክፍል አንድ ....................................................................................................2

ጠቅላላ ድንጋጌዎች .........................................................................................2

አንቀጽ አንድ- አጭር ርዕስ ...............................................................................2

አንቀጽ ሁለት- ትርጓሜ......................................................................................2

አንቀጽ ሶስት- የጾታ አገላለጽ ..............................................................................4

አንቀጽ አራት- የመመሪያው ዓላማ .......................................................................4

አንቀጽ አምስት- የአሰራር መርሆዎች ...................................................................4

አንቀጽ ስድስት- የተፈፃሚነት ወሰን ......................................................................5

ክፍል ሁለት.....................................................................................................5

የተኪ አመራር ምልመል መስፈርት፣ ሂደትና ቋት ማደራጀት ........................................5

አንቀጽ ሰባት- የተኪ አመራር ቋት ለማደራጀት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ................6

አንቀጽ ስምንት- የተኪ አመራር ምልመላ ሂደት .......................................................5

አንቀጽ ዘጠኝ- የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ሂደት ...............................................7

አንቀጽ አስር- የተኪ አመራር መረጃ ቋት ስለመከለስ ...............................................7

ክፍል ሶስት.....................................................................................................7

በተኪ የአመራር ቋት የማደራጀት ስራ ላይ የሚሳተፉ አካላት ያላቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት.....................................................................................................7

አንቀጽ አስራ አንድ- ብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት ..............7

አንቀጽ አስራ ሁለት- በየደረጃዉ የሚገኙ የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ......8

ክፍል አራት...................................................................................................10

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች .......................................................................................10

አንቀጽ አስራ ስድሰት- የሴቶች እና ወጣት ክንፍ አባላትን ተኪ አመራር ስለማድረግ ....................................................................................................10
አንቀጽ አስራ ሰባት- ከተኪ አመራር ቋት ስለመታገድ ..........................................11
አንቀጽ አስራ ስምንት- ቅሬታ ስለማቅረብ እና የሚስተናገድበት ሁኔታ ....................11
አንቀጽ አስራ ዘጠኝ- መመሪያውን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር............................11
አንቀጽ ሃያ- የመመሪያው ተፈፃሚነት ጊዜ .............................................................11

**መግቢያ**

በአገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ራዕይን እውን ለማድረግ በአስተሳሰባቸው፣ በስነ ምግባራቸው፣ በእውቀታቸው፣ በክህሎታቸውና በአፈፃፀም ብቃታቸው የላቁ አመራሮችን በየደረጃው በተኪ አመራር ቋት ለማደራጀትና ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የአመራር ሥርዓት መፍጠር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ጠንካራ የአመራር ሥርዓት ለመፍጠር መሰረታዊ ከሆኑ ጉዳዮች አንድ በፓርቲው ውስጥ ወደ አመራርነት የሚመጡ አካላት ብቃት ወሳኝ ሲሆን እነዚህን አካላት ለመለየት የሚያስችል አሰራር በፓርቲ ደረጃ ግልፅ በሆነ አግባብ ተቀርፆ ስራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣

በፓርቲው ውስጥ ለሚካሄደው የአመራር መተካካት ሂደት ስርዓት ለማበጀትና በየእርከኑ ተኪ አመራር ሆነው የሚመለመሉ አካላትን በግልፅ፣ ፍትሃዊ፣ አሰታፊና ተጠያቂነት ባለው ሂደት እንዲለዩ በማድረግ ስራውን ተቋማዊና ቀጣይነት ባለው መልኩ በውጤታማነት ማከናወን በማስፈለጉ፣

የተኪ አመራር ምልመለ ሂደት፣ የምልመላ መስፈርት፣ የተኪ አመራር ስምሪት እና የባለድርሻ አካላት ሚና በግልጽ በመደንገግ በፓርቲው ውስጥ ከላይ እስከ ታች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበር ለማድረግ፣ እንዲሁም በሂደቱ ለሚፈጠሩ ክፍተቶች የተጠያቂነት ስርዓትን ማስፈን በማስፈለጉ፣

በፓርቲ ውስጥ የአመራር ቀጣይነትን ለማረጋገጥና ወቅቱ ለሚፈልገው የትግል መድረክ ብቁ የሆኑ ተኪ አመራሮችን በመለየት የአመራርነት ብቃታቸውን ሊያሳድጉ የሚያስችሉ አቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 42 መሰረት የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራን ለማካሄድ ያስችል ዘንድ ይህ የተኪ የአመራር ቋት መመሪያ ተዘጋጅቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ አንድ- አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የብልጽግና ፓርቲ የተኪ አመራር ምልመላ ማስፈፀሚያ መመሪያ" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

**አንቀጽ ሁለት- ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ክልል"** ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል
2. **"ዞን"** ማለት ለክልል ተጠሪ የሆኑ የዞን አስተዳደሮች፣ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች እና በዞን ደረጃ ያሉ ከተሞችን እና ልዩ ወረዳዎችን የሚያጠቃልል ነው።
3. **"ወረዳ"** ማለት በክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የወረዳ ደረጃ የተሰጣቸው የአስተዳደር አካላትን ያጠቃልላል።
4. **"አስተባባሪ ኮሚቴ"** ማለት የፓርቲና የመንግስት ሥራዎችን አቀናጅቶ በበላይነት የሚያስተባብር እና በፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በተግባር ላይ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው አደረጃጀት ነው።

5. **"የፓርቲ አመራር ኮሚቴ"** ማለት የዋና ጽ/ቤትን ጨምሮ በየደረጃው በብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓርቲ ስራዎችን አቀናጅቶ የሚመራ፣ የሚያስፈጽምና የሚፈጽም የአመራር ኮሚቴ ማለት ነው፡፡
6. **"አመራር"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ አባል የሆኑ እና በፓርቲዉ አማካኝነት በመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ በየደረጃው ባለው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች፤ በመሰረታዊ ድርጅት፤ ህዋስ እና በልዩ ልዩ የአመራርነት ቦታዎች በሹመት፣ በምደባ ወይም በምርጫ ሃላፊነት የተሰጣቸዉ የፓርቲዉ አባላት ናቸው።
7. **"አባል"** ማለት የብልፅግና ፓርቲን መተዳደሪያ ደንብ እና ፕሮግራምን ተቀብሎ የአባልነት መብትና ግዴታውን የሚወጣ የፓርቲዉ አባል ማለት ነዉ።
8. **"የብልፅግና ህብረት"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና ከ22 እስከ 210 አባላትን ያቀፈ የብልፅግና ቤተሰብ ስብስብ የሆነ አደረጃጀት ማለት ነው፡፡
9. **"የብልፅግና ቤተሰብ"** ማለት ከ11 እስከ 35 አባላትን ያቀፈ ሆኖ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የአባላት የዕለት ተዕለት አቅም የሚገነባበት አደረጃጀት ነው፡፡
10. **"ግንባር ቀደም አባል"** ማለት ከአባላት መካከል በአመለካከታቸው፣ በስነ-ምግባራቸው፣ በተግባር እንቅስቃሴያቸው እና በአፈጻጸማቸው የተሻሉ ሆነው በአባላት ዘንድ እንዲሁም በአካባቢ ማህበረሰብ በአርአያነት የሚታዩ አባላት ማለት ነው፡፡
11. **"የአባል ባህሪይ"** ማለት የአንድ አባል አጠቃላይ የአስተሳሰብ፣ የስነ-ምግባር፣ የአመለካከት እና ድርጊት የጋራ ውጤት ነው፡፡
12. **"ተኪ አመራር"** ማለት የፓርቲ አባል ሆነው በግንባር ቀደም አባልነት የተለዩ እና የብልፅግና ህብረትና የብልፅግና ቤሰተብ አመራር ሆነው በቀጣይ በተለያዩ ደረጃዎች ለፓርቲና መንግስት ተልዕኮ ተኪ አመራር ሊሆኑ የሚችሉ አባላትና የፓርቲ አመራሮች ማለት ነው፡፡
13. **"የተኪ አመራር ቋት"** ማለት በየደረጃው ካለው የፓርቲ አደረጃጀት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ከተለዩት አባላት ወይም የብልፅግና ህብረትና የብልፅግና ቤተሰብ አመራር ሆነው በመስራት ካሉ አመራሮች መካከል በአስተሳሰባቸው፣ በስነ-

ምግባራቸውና በአፈጻጸም ብቃታቸው የተሻሉ ሆነው ለተኪ አመራርነት የተለዩት አመራሮች መረጃ ተደራጅቶ የሚቀመጥበት ባንክ ማለት ነው፡፡

14. **“መርህ አልባ ግንኙነት”** ማለት አንድ አመራር የግል ጥቅም ለማግኘት ወይም ሌላውን ለመጥቀም ወይም ሌላ እኩይ ዓላማን ለማሳካት ሲል ከፓርቲ መርሆዎችና እሴቶች ውጭ በሆነና ሕዝብን፣ ሀገርንና ፓርቲን በሚጎዳ መንገድ ከሌሎች አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች የሚያጠቃልል ነው፡፡

15. **“መልካም የፓርቲ ሥነ-ምግባር”** ማለት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተደነገጉ የአባልነት ግዴታ፣ የፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና አሰራሮችን ማክበርና በጥብቅ ዲስፕሊን መፈፀም እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚስማማባቸውን የግብረ-ገብ እሴቶችን ማክበርና መልካም ተግባራትን በመፈጸም አርአያ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ ሶስት- የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጹት ሃሳቦች በሙሉ የሴት ፆታን የሚያመላክቱ ይሆናል።

## አንቀጽ አራት- የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ ግልፅ፣ አሳታፊና ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የተኪ አመራር ቋትን በማደራጀት የፓርቲን አመራር ለማጠናከር ነዉ።

## አንቀጽ አምስት- የአሰራር መርሆዎች

ተኪ አመራሮችን በቋት የማደራጀት ስራ በሚከተሉት የአሰራር መርሆዎች የሚመራ ይሆናል።

1. የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራ እውነተኛ መረጃ እና ማስረጃን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራ አሳታፊ፣ አካታች፣ ከወገንተኝነት እና አድሎዓዊነት አሰራር ነፃ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. የምልመላ ሂደቱ በመፈፀም ብቃት ማዕቀፍ ውስጥ የሴቶች፣ ወጣቶች፣ ምሁራን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

4. የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ በየደረጃው ላሉ አደረጃጀቶች ግልፅ እና በግልጸኝነት አሰራርን የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። አሰራርን ያልተከተለ የተኪ አመራር ቋትን ማደራጀት ስራ ተጠያቂነትን ያስከትላል።
5. በአመለካከትና በተግባር አንድነት፣ ውጤታማነትና ግንባር ቀደም መሆን ይኖርበታል
6. የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራ ጥራቱን የጠበቀ፣ መፃኢ የፓርቲያችንን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ እና ለሚፈለገው ዓላማ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል።
7. የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ በአመራር ሥርዓታችን፣ በብቃት እና በህብረ-ብሔራዊነት መካከል ሚዛን ለማስጠበቅ የሚያስችል ሊሆን ይገባል።

### አንቀጽ ስድስት- የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በየደረጃው ከፌዴራል እስከ የብልፅግና ቤተሰብ ድረስ ባሉ የፓርቲ አደረጃጀቶች፣ አመራሮች እና አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የተኪ አመራር ምልመላ መስፈርት፣ ሂደት እና ቋት ማደራጀት

### አንቀጽ ሰባት- የተኪ አመራር ምልመላ ሂደት

የተኪ አመራር ምልመላው የብልፅግና ፓርቲ የተኪ አመራር ምልመላ በአንቀጽ 5 ላይ የተዘረዘሩ መርሆዎችን ተከትሎ ከዚህ ቀጥሎ በተቀመጡ ሂደቶች መሰረት ይፈጸማል፡፡

1. ከግንባር ቀደም አባላት መካከል ተኪ አመራሮች ሊሆኑ የሚችሉ በብልፅግና ቤተሰብ ተመልምሎ ለብልፅግና ህብረት ሪፖርት ይቀርባል፡፡
2. በብልፅግና ቤተሰብ የተመለመለውን ተኪ አመራር በብልፅግና ህብረት አባላት ኮንፈረንስ በማስተቸት ለአከባቢው ለሚገኘው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ከነሙሉ ፕሮፋይል ያቀርባል፡፡

3. በአከባቢ ያለው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አመራር ኮሚቴ ያጸድቃል ወይም ይመልሳል፡፡

**አንቀጽ ስምንት- የተኪ አመራር ቋት ለማደራጀት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች**

ተቋማዊ መሠረት ያለው፤ ከማንኛውም አድሏዊ አሠራር ነፃ የሆነ፣ ግልፅና ውጤታማ የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት በማስፈለጉ የሚከተሉት የምልመላ መስፈርቶች ተዘጋጅቷል፡፡

1. በፓርቲዉ መሰረታዊ እሳቤ ላይ ፅኑ እምነትና አቋም ያለው፤ በህብረ ብሔራዊነት እና በሀገራዊ አንድነት የሚያምን፤ የጠራ አመለካከት ያለው እና ፅንፈኝነትን በፅናት የሚታገል፤ ዜጎችንና ህዝቦችን በእኩልነት የሚያገለግል፣ የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድም፣ ከማንኛውም የሙስናና ብልሹ አሠራሮች እንዲሁም መልካም ካልሆነ ስነ-ምግባር ራሱን ያራቀና ሌሎችንም በመገንባት የተመሰከረለት፤ በዚህም በአባላትና በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ያተረፈ፤
2. አመራር ለመሆን ፍላጎት ያለው፣
3. ነባራዊ ሁኔታዎችን ቶሎ የመረዳትና የሚሰጠውን አቅጣጫ የመቀበል ችሎታ ያለው፣
4. ሀሳቡን አደራጅቶ ለመግለፅ ሙሉ ነፃነት የሚሰማውና የሌሎችን ሀሳብ ለማስተናገድ የሚያስችል ዴሞክራሲያዊ ስብዕና ያለው፤
5. በሥራ ሂደት ለሚያጋጥሙ አስቸጋሪ ፈተናዎችን የመጋፈጥ ድፍረት ያለውና በአሸናፊነት የመውጣት ብቃት ያለው፤
6. ከሥራው ጋር የተያያዘ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ ፤
7. በተሰማራበት የስራ መስክ በተግባር አፈጻጸም ለሌሎች አባላት አርአያ መሆን የቻለ፡፡
8. በየደረጃው ከሚመለመሉት አመራሮች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ቢያንስ ሰላሳ ፐርሰንት (30%) መሆን ይኖርበታል።
9. ለተኪ አመራር የሚመለመለው ዕድሜው 18 እሰከ 50 ዓመት ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡

10. ምልመላው ከወረዳ ጀምሮ እስከ ፌደራል ተኪ አመራር ሊሆኑ የሚችሉ ግንባር ቀደሞችን የሚያካትት ሆኖ አካል ጉዳተኞች ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

11. በአባላትና አደረጃጀቶች ምዘና መሰረት በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ይጠበቅበታል፡፡

12. ለአባላት በሚሰጠው ስልጠና ውስጥ ያለፈ መሆን ይኖርበታል፡፡

13. በፓርቲው እሳቤው ላይ የሚሰጠውን ፈተና 65 ፐርሰንት እና ከዚያ በላይ ማምጣት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ- የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ሂደት

1. ከላይ በአንቀጽ ሰባት በተገለጸው መሰረት በየደረጃው የተመለመሉ ተኪ አመራሮች ዝርዝር መረጃ በየደረጃው ባለው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች እና በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ደረጃ ለአጠቃቀም ምቹ በሆነ ሁኔታ የሚደራጅ ይሆናል፡፡
2. በየደረጃው የተደራጀው የተኪ አመራሮች ዝርዝር የተኪ አመራሮች ባንክ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
3. የተኪ አመራሮችን ቋት የማደራጀት ስራ በየሩብ አመቱ በየደረጃው ባሉ የቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስር- የተኪ አመራር መረጃ ቋት ስለመከለስ

በየደረጃው የተደራጀው የተኪ አመራር መረጃ ቋት ተደራሽ፣ ወቅታዊ እና ተአማኒ እንዲሆን በአመት ሁለት ጊዜ መከለስ አለበት።

# ክፍል ሶስት

# በተኪ የአመራር ቋት የማደራጀት ስራ ላይ የሚሳተፉ አካላት ያላቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት

## አንቀጽ አስራ አንድ- የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ፣ ከነባሩ የመረጃ ቋት ጋር የተቀናጀ የተኪ አመራር መረጃ ቋት ያለማል፣

2. ለክልሎች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በተኪ አመራር ቋት ስራ ዓላማ፣ አፈጻጸም ሂደት ላይ ስልጠና ይሰጣል፤
3. ለክልሎች የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች አመራርና ባለሙያዎች የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና ይሰጣል እና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በቴክኖሎጂ ግብአት ያበለጽጋል፤
4. ለክልሎች ተግባር ተኮር ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል እና ግብረ መልስ ይሰጣል፤
5. ከክልሎች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የሚላከዉን መረጃ ያጣራል፤ በአግባቡ ያደራጃል፤ ያስተዳድራል ለታለመለት ዓላማ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

## አንቀጽ አስራ ሁለት- በየደረጃዉ የሚገኙ የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. በየደረጃዉ ለሚገኙ ፓርቲ አመራሮች በተኪ አመራር ቋት ስራ ዓላማ፣ የአፈጻጸም ሂደት ላይ በየጊዜዉ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፤
2. ከታችኛዉ ፓርቲ መዋቅር ተመልምለው የሚላኩ የተኪ አመራር መረጃዎች በመስፈርቱ መሰረት መሆኑን ይከታተላሉ፣ ይደግፋሉ፣ ይገመግማሉ፣ ግብረ-መልስ ይሰጣሉ፣ ትክክለኛነቱን ያረጋግጣሉ።
3. የተኪ አመራር ቋት ስራ በተቀመጠዉ የጊዜ ሠሌዳ መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋሉ።
4. የተመለመሉ የተኪ አመራሮችን በአመራር ቋት ውስጥ ያደራጃሉ፤ አንድ ደረጃ ከፍ ላለዉ የፓርቲ መዋቅር በሪፖርት ያሳዉቃሉ፤
5. በክትትል ሂደት ድክመት የታየባቸው ተኪ አመራሮች ሲያጋጥሙ ጉዳዩን በማጣራት ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር በማስደገፍ ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት በማቅረብ ከተኪ አመራር ቋት እንዲወጡ ያደርጋል፣ ከመረጃ ቋት ይሰርዛል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሶስት- የብልፅግና ህብረት ተግባርና ኃላፊነት

1. በአባላት ተሳትፎ ከብልፅግና ቤተሰብ የተመለመሉ ግንባር ቀደም አባላት በምልመላ መስፈርቱ የተለዩ መሆናቸውን ወይም ትክክለኛነቱን በማጣራት ለአባላት ኮንፈረንስ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡
2. የፀደቀውን የተኪ አመራሮች ሙሉ ፕሮፋል በቅርበት ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

3. በየጊዜው ከበላይ ተለይተው የሚመጡላትን ተኪ አመራሮች ዝርዝር በሚቀጥለው ኮንፍረንስ መርምሮ የማጽደቅ ስራ ይሰራል፡፡
4. የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት የጸደቁ የተኪ አመራሮችን እንቅስቃሴ በንቃት ይከታተላል በየ ስድስት ወሩ በተኪ አመራርነት ስለመቀጠላቸው ይሁንታ ይሰጣል፡፡
5. በክትትል ሂደት ድክመት የታየባቸው ተኪ አመራሮች ሲያጋጥሙ ጉዳዩን በማጣራት ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር በማስደገፍ ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት በማቅረብ ከተኪ አመራር ቋት እንዲወጡ ያደርጋል፡፡
6. ከተኪ አመራርነት ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት- የብልፅግና ቤተሰብ ተግባርና ኃላፊነት

1. የመደበኛ የአባላት የግምገማ ወይም የምዘና ስርዓትን ተከትሎ ቢያንስ በስድስት ወር አፈጻጸማቸው ግንባር ቀደም የሆኑ አባላትን እየለየ ለብልፅግና ቤተሰብ ያሳውቃል፡
2. ከብልፅግና ቤተሰብ አባላት በተኪ አመራርነት ተይዘው ያሉትን አባላት የዘወትር ክትትል በማድረግ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤ ችግር ያለባቸው ሲጋጥሙ ለብልፅግና ህብረት ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት- የተለዩ ተኪ አመራሮች ስለመጠቀም

1. በሁሉም እርከን ፓርቲ ያለውን የሰው ሃይል አቅምና ተነሳሽነት አውቆ ለተልዕኮ ዝግጁ ለማድረግ ይጠቀምበታል፡፡
2. በግምገማ፣ በተግባር አፈጻጸም፣ በስነ-ምግባር እንዲሁም በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ የአመራር ጉድለት ሲያጋጥም በጥንቃቄ አመራር ለመተካት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
3. ከአሰራር ውጭ በተለምዶ አመራር የመተካት ሂደቶች እንዲቀሩና ፓርቲው የጠንካራ አመራር ስብስብ እንዲሆን በማድረግ ውጤታማነቱን ለማሳደግ ያግዛል፡፡
4. የተኪ አመራር ምደባው በአመራር ምደባ መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

5. ተኪ አመራር የመተካት ሂደት በተኪ አመራር ቋት ከተያዙት መካከል በአመራር ምደባ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡
6. በተኪ አመራር ፑል ካልተያዘ በስተቀር ወይም በልዩ ሁኔታ ከሙያ ጋር ተያይዞ መተካት ወይም የሚመደብ  አመራር ካልሆነ በስተቀር ከተኪ አመራር ቋት ውጭ በተለምዶ አመራር መመደብ ክልክል ነው፡፡
7. በተለያዩ ምክንያቶች አመራርን በተኪ አመራር መተካት በሚያስፈልግበት ወቅት በተኪ አመራርነት የተመለመሉ ሴት እና ወጣት አመራሮች ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ አስራ ስድሰት- የሴቶች እና ወጣት ክንፍ አባላትን ተኪ አመራር ስለማድረግ

1. በዚህ መመሪያ መሰረት የተኪ አመራርነትን ምልመላ መስፈርት የሚያሟሉ የብልጽግና ሴቶች ክንፍና እድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የብልጽግና ወጣቶች ክንፍ አባላት ተኪ አመራር ሆነው ሊመለመሉ ይችላሉ፡ ፡
2. በዚህ የተኪ አመራር ምልመላ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ የብልጽግና ክንፍ አባላት በክንፎቹ የአደረጃጀት እርከን ተመርጠው ለሚንቀሳቀሱበት የአከባቢ ቅ/ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡
3. የተኪ አመራር ምልመላው የቀረበለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት የቀረበለትን ዝርዝር መስፈርቱን እና ሂደቱን የጠበቀ መሆኑን በመመርመር በየደረጃው ባለው የፓርቲ አመራር ኮሚቴ  እንዲፀድቅ ያደርጋል፡፡
4. በደረጃው ያለው የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት በአመራር ኮሚቴው የጸደቀውን ዝርዝር በተኪ አመራር ቋት ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡
5. በአመራር ቋት ውስጥ የገባ የተኪ አመራር ክንፍ አባላት ቀጥሎ የሚኖረው አጠቃላይ  እንቅስቃሴ በየደረጃው በክንፉ መዋቅር አማካኝነት ክትትል

የሚደረግ ሆኖ በየሶስት ወሩ ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

6. መመሪያውን ሳይጠብቅ የሚከናወን ምልመላ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ ከጅልም ያሰርዛል፡፡

**አንቀጽ አስራ ሰባት- ከተኪ አመራር ቋት ስለመታገድ**

1. ማንኛውም በተኪ አመራር ቋት የተያዘ አባል የአፈፃፀም ድክመት፣ የዲሲፕሊን ግድፈት፣ የብልሹ አሰራር እና የሰርጎ ገብነት ችግር ያለበት መሆኑ በግምገማ የተረጋገጠበት ከሆነ ከተኪ ቋት የሚታገድ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ አንድ አመራር በራሱ ፍቃድ ከአመራር ቋት ሊወጣ ይችላል።

**አንቀጽ አስራ ስምንት- ቅሬታ ስለማቅረብ እና የሚስተናገድ ሁኔታ**

በየደረጃው በሚካሄደው የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራ ላይ ቅሬታ ያላቸው አባላት በብልጽግና ፓርቲ የአመራርና የአባላት የዲሲፕሊን መመሪያ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መሰረት ቅሬታቸውን በማቅረብ መስተናገድ ይችላሉ።

**አንቀጽ አስራ ዘጠኝ- መመሪያውን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር**

ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የብልፅግና ፓርቲ ምክር ቤት ሊያሻሽለው ወይም ሊቀይረው ይችላል።

**አንቀጽ ሃያ- መመሪያው የሚፀናበት**

ይህ መመሪያ በብልጽግና ፓርቲ ምክር ቤት ከጸደቀበት ከመያዚያ 2016 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

**ዐብይ አህመድ(ዶ/ር)**

**የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት**

**መያዚያ 2016 አ.አ**